# መልክዐ ቅዱስ ዳዊት

| መልክዐ ቅዱስ ዳዊት-ግእዝ | የቅዱስ ዳዊት መልክዕ በአማርኛ |
|---|---|
| ፩. እምሥርወ እሴይ ዘሠረፀከ ወእማሕፀና ለሩት፤ ያስተበጽዑከ በእንተዝ በጥበበ ኵሉ ስብሐት፤ ኦ ብፁዕ ንጉሠ እስኤል ዳዊት፤ እስመ ተረክበ ወተከሥተ ባሕርየ ኀቡዕ ሕይወት፤ እመዝገበ ከርሣ ለማርያም ዘለከ ወለት፡፡ | 1. እምሥርወ እሴይ፡- ከልጅህ ከድንግል ማርያም ማሕፀን የማይመረመር የሕይወት ባሕርይ ፈጽሞ ተገኝቷልና ከእሴይ አብራክ እና ከሩት ማሕፀን ተገኘህ፤ ስለዚህ በምሥጋና ጥበብ ሁሉ ‹የእስራኤል ንጉሥ ክቡር ዳዊት› እያሉ ያደንቁሃል፡፡ |
| ፪. ሰላም ለዝክረ ስምከ ውስተ ፈትለ መዝሙር ዘተወሐደ፤ ወለሥዕርትከ ሰላም በቅብዐ ትሕትና ዘጽሕደ፤ ፍኖተ ሰማይ ዳዊት ጊዜ አርታዕከ መንገደ፤ አስተፋጥን ለቀበላየ እንዘ ታስተሴኒ እደ፤ እስመ ፍና ዝንቱ መፅብብ ያፈርህ ፈድፋደ፡፡ | 2. ለዝክረ ስምከ፡- በትሕትና ቅባት ለለዘበ ጠጕርህ እና በምስጋና ፈትል ውስጥ አንድ ለሆነ ለስምህ መታሰቢያ ሰላምታ ይገባል፤ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ወደ ሰማይ ጐዳና መንገድን በአቀናህ ጊዜ ይኽ ጠባብ መንገድ እጅግ ያስፈራልና እጅህን እያዘጋጀህ እኔን ለመቀበል አፍጥን፡፡ |
| ፫. ሰላም ለርእስከ በአክሊለ መንግሥት ዘከብረ፤ ወለሥነ ገጽከ እምፀሐይ ዘይበርህ ወትረ፤ ለኀበ ሰማይ ዳዊት ጊዜ አርታዕከ ሐዊረ፤ አስተሳኒ ሊተ መሰንቆ ወአስተዋድድ መዝሙረ፤ ከመ ለጻድቃን ታስተዴሉ ምዕረ፡፡ | 3. ለርእስከ፡- ከፀሐይ ይልቅ ዘወትር እጅግ ለሚያበራ ለፊትህ ደም ግባት እና በመንግሥት ዘውድ ለከበረ ራስህ ሰላምታ ይገባል፤ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ወደ ሰማይ ለመሔድ በአቀናህ ጊዜ ለጻድቃን ፈጽመህ እንደምታዘጋጅ መዝሙርን አስማማ፤ መሰንቆንም አሳምር፡፡ |
| ፬. ሰላም ለቀራንብቲከ ወለአዕይንቲከ እለ ኵሕል፤ ወለአእዛኒከ ርኁባት ጊዜ አጽምአ ፍትሐ ወቃል፤ ርኁቀ በቀል ዳዊት ንጉሠ እስራኤል፤ ፀርየ ቅትል እግዚኦ በመጥባሕትከ ስሑል፤ አምጣነ ሰይጣን ውእቱ ኀልያድ ኃያል፡፡ | 4. ለቀራንብቲከ፡- ቃልንና ፍርድን በመስማት ጊዜ ለተራቡ ጆሮዎችህ፣ ለተዋቡ ቅንድቦችህ እና ለዐይኖችህ ሰላምታ ይገባል፤ የእስራኤል ንጉሥ የዋህ በቀልን የማታውቅ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ኃይለኛ ጐልያድ ሰይጣን ነውና አቤቱ በተሳለ ሰይፍህ ጠላቴን ግደለው፡፡ |
| ፭. ሰላም ለመላትሒከ ዘስኂን አምሳለ ሮማን፤ ወለአእናፊከ ምዑዛት እምጼና ሐንክሶ ወልብን፤ ዳዊት ብፁዕ ንጉሠ ቤርሳቤሕ ወዳን፤ ኢይትዓበይ በላዕሌየ ጎልያድ ሰይጣን፤ እደ ጸሎትከ ይቅትሎ በዕብን፡፡ | 5. ለመላትሒከ፡- ከከበረ ሽቱ ይልቅ ለሚጣፍጡ አፍንጫዎችህ እና በሮማን አምሳል መልካም መዓዛ ለአለው ጕንጭህ ሰላምታ ይገባል፤ የዳንና የቤርሳቤህ ንጉሥ ብፁዕ ዳዊት ሆይ! ጐልያድ ሰይጣን በእኔ ላይ እንዳይኮራ የጸሎት እጅህ በድንጋይ ይግደለው፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፮. ሰላም ለከናፍሪከ መሰንቆ ሃይማኖት ዘነበባ፤ ምስለ አፉከ ስብሐተ እንዘ ያቈርባ፤ ዳዊት ለጽዮን ንጉሠ ሕዝባ፤ ዕጣነ ስኂን ወወርቅ ነገሥተ ተርሴስ ወሳባ፤ ያበውኡ ለወልድከ ለኦሪት በምግባ። | 6. ለከናፍሪከ፡- ከአፍህ ጋር ምስጋናን እያቀረቡ የሃይማኖት መሰንቆን ለተናገሩ ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ የጽዮን ሕዝብ ንጉሥ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! የሳባ እና የተርሴስ ነገሥታት ወርቅና ከርቤ ዕጣን ለልጅህ በኦሪት ሥርዐት ያቀርባሉ። |
| ፯. ሰላም ለአስናኒከ ወለልሳንከ መክብቡ፤ ጊዜ ቃልከ ነበበ በዘይሤኒ ንባቡ፤ የዋህ ልቡና ዳዊት ለእግዚአብሔር ቅርቡ፤ በሎሙ በመዝሙርከ ለሕዝበ እስራኤል የብቡ፤ አምጣነ ተከሥተ ሊተ ለክርስቶስ ጥበቡ። | 7. ለአስናኒከ፡- ንንግሩ ለሚያምር አንደበትህ እና በተናገርህ ጊዜ ለአንደበትህ ጌጥ ለሆነ ጥርስህ ሰላምታ ይገባል፤ ልብህ የዋህ የሆነ ለእግዚአብሔር የምትቀርብ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ‹የክርስቶስ ምሥጢሩ ተገልጦልኛልና የእስራኤልን ሕዝቦች በመዝሙርህ እልል በሉ› በላቸው፡ |
| ፰. ሰላም ለእስትንፋስከ በመዓዛ ዐልው ዘተቶስሐ፤ ወለጐርኤከ ዘሰትየ ወይነ አእምሮ ፍሉሐ፤ ለኵልነ ሀሊ አርከ ፈጣሪ ምሕረተ ወፍትሐ፤ ከመ ንትሉ በአሠርከ ፍኖተ ንጹሐ፤ ወንኩን ከማከ ለገቢር ንስሓ። | 8. ለእስትንፋስከ፡- የበሰለ የዕውቀትን ወይን ለጠጣ ጉሮሮህ እና በሽቱ መዓዛ ላይ ለተጨመረ እስትንፋስህ ሰላምታ ይገባል፤ የፈጣሪ ወዳጅ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! በጐዳናህ ንጹሕ መንገድን እንከተል ዘንድ ንስሐን ለማድረግ እንደ አንተ እንሆን ዘንድ ምሕረትንና ፍርድን ለሁላችን ዘምር (ለምንልን)። |
| ፱. ሰላም ለቃልከ ሥርግወ ትንቢት አምሳለ ቃማ፤ ወለመትከፍትከ ግልቡብ በልብሰ ሞገስ ወግርማ፤ ንጉሠ እስራኤል ዳዊት ዘሐፀነተከ አውቴ ዝራማ፤ እፎ ተበጽአ ትሕትናከ በልሳነ ንጉሥ ዘራማ፤ ሶበ ኀደገ አፍቅሮታ ለዓለም ዘማ። | 9. ለቃልከ፡- በባለሟልነት እና በመወደድ ልብስ ለተሸፈነ ትከሻህ እና በወርቅ አምሳያ ትንቢትን ለተሸለመ ቃልህ ሰላምታ ይገባል፤ አውቴ ዝራማ ያሳደገችህ የእስራኤል ንጉሥ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! የዘማዊት ዓለምን መውደድ በተውህ ጊዜ በሰማይ ንጉሥ አንደበት ትሕትናህ እንዴት ተደነቀ! |
| ፲. ሰላም ለዘባንከ ወለእንግድዓከ ቢጹ፤ ለብርሃነ ኂሩት ወተግሣጽ በጽርሐ ጥበባት ሐነፁ፤ ርኁቀ በቀል ዳዊት ለቅብዐ መንግሥት አንቀጹ፤ ለፀርየ አእጋሪሆሙ ጸሎታቲከ ያእቅፁ፤ ወከመ ማኅረጽ ርእሶሙ ይህርፁ። | 10. ለዘባንከ፡- ለቸርነት ብርሃንና ተግሣጽ የጥበባት አዳራሾችን ለሠሩ ለጀርባህ እና ለደረትህ ሰላምታ ይገባል፤ ከበቀል የራቅህና የቅብዐ መንግሥት መጀመሪያ የሆንህ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! የጠላቶቼን እግራቸውን ጸሎትህ ያሰናክለው፤ በጸሎትህም ኃይል እንደ ወፍጮ ራሳቸውን ይፍጩ። |
| ፲፩. ሰላም ለሕፅንከ ወለአዕዳዊከ ኀቡረ፤ ለብርአ ጥበቡ ለአምላክ እለ ጸሐፉ መዝሙረ፤ ልዑለ ትሕትና ዳዊት እንተ ተጸጕከ ክብረ፤ እንዘ ትብል ብፁዕ ብእሲ በምክረ ረሲዓን | 11. ለሕፅንከ፡- በአምላክ ጥበብ ብዕር ምስጋናን በአንድነት ለጻፉ ለእጆችህ እና ለጭንህ ሰላምታ ይገባል፤ ክብርን የተሰጠህ በትሕትና ከፍ ያልህ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ‹በጕስቋሎች ምክር ያልኖረ ሰው ብፁዕ ነው፤ |

| | |
|---|---|
| ዘኢሖረ፤ ወሕገ አምላኩ ርቱዐ ዘይነብብ ወትረ፡፡ | የቀና የአምላክን ሕግም ዘወትር የሚፈጽም ብፁዕ ነው› በለን፡፡ |
| ፲፪. ሰላም ለመዛርዒከ ለቀቲለ ግሩም አንበሳ፤ በኃይለ ሡርናዕከ ዘጸንዐ እምጽንዓ ኃያላን ስሳ፤ ኅሩየ አምላክ ዳዊት ወለክብረ መንግሥት ሞገሳ፤ ጽዮን አመ እትወታ ምድረ ኢሎፍሊ ገይሳ፤ ትኤምኃከ እንዘ ትብል ሐዊሳ፡፡ | 12. ለመዛርዒከ፦ ከስልሳ ኃይለኞች ጽናት ይልቅ ለጸና በክርንህ ኃይል አስፈሪ አንበሳን ለገደለ መዝራዕትህ ሰላምታ ይገባል፤ አምላክ የመረጠህና ለመንግሥት ክብር ባለሟል የሆንህ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ከኢሎፍሊ ምድር ገሥግሣ ጽዮን በምትገባ ጊዜ በደስታና በአንክሮ የሰላምታ ቃል ‹ንጽሕና ሆይ! መጣህን› እያለች እጅ ትነሣኻለች፡፡፡ |
| ፲፫. ሰላም ለእመትከ ወለእራኅከ መፍቅድ፤ ዘመሰንቆ ማኅሌት ይጼውዕ እምታሕተ አፃብዕ ውዱድ፤ መሠረት ሰላም ዳዊት ወለቃለ መዝሙር ድድ፤ ምስሌየ ሀሉ እግዚእየ እስከ የኃልፍ ትውልድ፤ እስመ አነ ከመ ሡሉ ፈላሲ ወነግድ፡፡ | 13. ለእመትከ፡- የምስጋና መሰንቆን ተአዘጋጅ ዘንድ ከጣቶች በታች ለተስማማና ለተወደደ ለመሐል እጅህ እና ለክንድህ ሰላምታ ይገባል፤ የሰላምና የምስጋና ቃል መሠረት ቅዱስ ዳዊት ሆይ! እኔ እንደ ሁሉ ስደተኛና እንግዳ ነኝና ትውልድ እስኪያልፍ ድረስ ጌታየ ሆይ! ከእኔ ጋር ኑር፡፡ |
| ፲፬. ሰላም ለአጽፋረ እዴከ ወለገቦከ ስኩብ፤ በዘባነ መንግሥት ቅድው ዘሐሳበ ሜጡ ዕፁብ፤ የዋሀ ሕሊና ዳዊት አምሳለ የዋሂት ርግብ፤ ብእሴ ረከብኩ ዘከማየ እምነገደ አእላፍ ሕዝብ፤ በቃለ ዚአሁ ይብለከ አምላክነ አብ፡፡ | 14. ለአጽፋረ እዴከ፡- ዋጋው ድንቅ በሆነ በሚያምር መንግሥት ጀርባ ለተኛ ጐንህ እና ለእጅህ ጥፍሮች ሰላምታ ይገባል፤ በየዋሂት ርግብ አምሳል ሀሳብህ የዋህ የሆነ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! አምላካችን አብ በቃሉ ‹ከብዙ ሕዝብ ወገን መካከል እንደ እኔ ያለ ሰውን አገኘሁ› ይልኻል፡፡ |
| ፲፭. ሰላም ለከርሥከ እምብዕለ ቅንዓት ግሁስ፤ ወለልብከ ሰላም ምሉዓ ቅዱስ መንፈስ፤ አስተበፅዐከ ዮም ዳዊት ንጉሥ፤ ታንጽሐኒ በጸሎትከ እምርስሐተ ጌጋይ ርሡስ፤ እስመ ሕማማ ወሞታ ለነፍስ፡፡ | 15. ለከርሥከ፦ መንፈስ ቅዱስን ለተመላ ልብህ እና ከቅንዓት ገንዘብ ለራቀ ሆድህ ሰላምታ ይገባል፤ ልበ አምላክ ንጉሥ ዳዊት ሆይ! ለነፍስ ሕማሟና ሞቷ ነውና ከረከሰ የበደል ጉስቁልና በጸሎትህ ታነጻኝ ዘንድ ዛሬ አመሰግንኻለሁ፡፡ |
| ፲፮. ሰላም ለሡልያቲከ ወለአማዑቲከ ምዕላደ ትንቢት ወሕግ፤ ወለሕሊናከ ሰላም ዘማየ ርኅራኄ ፈለግ፤ ማዕደ አምላክ ዳዊት በማዕጸ ትሕትና ንሱግ፤ እምሰምሶን ቀታሊ እልፍ በመንሰከ ድኩም አድግ፤ ትኄይስ አንተ ወትጸንዕ እምኅግ፡፡ | 16. ለሡልያቲከ፡- የርኅራኄ ውኃ ምንጭ ለሆነ ሀሳብህ እና የትንቢትና የሕግ መከማቻ ለሆነ አንጀትህ እና ሡላሊትህ ሰላምታ ይገባል፤ በትሕትና መዝጊያ የዘጋህ የአምላክ ማዕድ ዳዊት ሆይ! በደካማ አህያ መንጋጋ እልፍ ከገደለ ከሶምሶን ይልቅ አንተ ትሻላለህ፤ ከብዙዎችም አንተ ትጸናለህ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፲፯. ሰላም ለኀንብርትከ ለአካልከ ማዕከሉ፤ በበመክፈልተዝ ሐቌከ ወለአቀ፝ያጺከ ክፍሉ፤ አምላኩ ለሙሴ ዘወደሰከ በቃሉ፤ እንዘ ይብል ከመ ልብየ እምነ ፍጡራን ኵሉ፤ ረከብኩ ዳዊትሃ ዘንኡስ አካሉ፡፡ | 17. ለኀንብርትከ፡- ለጭኖችህ ክፍሎች እና በጀርባህ ክፍል አካልህ መካከሉ ለሆነ እምብርትህ ሰላምታ ይገባል፤ የሙሴ አምላክ ‹ከፍጡራን ሁሉ እንደ ልቤ የሆነ በሰውነቱ ትንሽ የሆነ ዳዊትን አገኘሁ› እያለ አመሰገነህ፡፡ |
| ፲፰. ሰላም ለአእጋሪከ እለ ጸንዓ ከመ ኀያል፤ አምሳለ ረዋጺ ወይጠል፤ ወከመ ከማሃ ለጽዮን በውሳጤ ሐዲስ ምርጡል፤ ታስተበጽአከ በንባበ ቃላ ዘይብል፤ ዳዊት ትሑት ወዳዊት ልዑል፡፡ | 18. ለአእጋሪከ፡- በሚሮጥ ፌቆ አምሳያ እንደ ዋልያ ለበረቱ እግሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ‹እንደ ጽዮን በአዲስ አዳራሽ ውስጥ ዳዊት ከፍ ያለ ነው፤ ዳዊት ትሑት ነው› እያለች በቃሏ ንግግር ታደንቅኻለች፡፡ |
| ፲፱. ሰላም ለሰኰናከ ወለመከየድከ ክልኤቱ፤ እለ አጽንአ ቀዊመ ለአምላክ በፍኖቱ፤ ስምከ ዳዊት ማኅየዊ በኀበ ሥላሴ ሠለስቱ፤ ወዝክረ ስምከ በአርጋኖን ዘአውታሪሁ ዐሥርቱ፤ ወበቅድመ እግዚአብሔር ለጻድቅ ክቡር ሞቱ፡፡ | 19. ለሰኰናከ፡- በአምላክ ጐዳና ጸንተው ለቆሙ ለሁለቱ መረገጫዎችህ እና ለተረከዝህ ሰላምታ ይገባል፤ የአምላክ ልብ የተባልህ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ስምህ በሥሉስ ቅዱስ ዘንድ ሕያው ነው፤ አውታሩ ዐሥር በሆነ ምስጋና ለስምህ መታሰቢያ ሆነ፤ የጻድቅ ሞት በእግዚአብሔር ፊት ክቡር ነው፡፡ |
| ፳. ሰላም ለአፃብዒከ ዘበፍና አእጋር ኢተአቅፉ፤ ልብሰ ወልታ አጽፋር ፀዓድው እንዘ ይተአጸፉ፤ ዳዊት በለኒ ለቃለ መዝሙር ለለምዕራፉ፤ አእጋረ ነፍስየ ድኩማን አመ ፍና ሰማይ ኀለፉ፤ ዘጻመወ በዓለም የሐዩ ለዝሉፉ፡፡ | 20. ለአፃብዒከ፡- ነጭ የሆኑ የጥፍሮች ጋሻ ልብስን እየተጐናጸፉ በእግር መንገድ ለአልተሰነካከሉ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ ነቢየ ልዑል ቅዱስ ዳዊት ሆይ! በምስጋናህ ቃል በየምዕራፍ ደካማ የሆኑ የነፍሴ እግሮች በሰማይ ጐዳና በሔዱ ጊዜ ‹በዓለም የደከመ ለዘለዓለም ይድናል› በለኝ፡፡ |
| ፳፩. ሰላም ለቆምከ ዘበአብቋሉ ሠናይ፤ ወለመልክዕከ ጽጌ ከመ ሠርቀ ቲቶ ፀሐይ፤ ዳዊት ንጉሥ ዳዊት ነቢይ፤ ትክለኒ በጸሎትከ ከመ ሥሙረ ዕፅ ዘማይ፤ ውስተ ገነትከ ዘቅፅራ ባሕርይ፡፡ | 21. ለቆምከ፡- እንደ መስከረም መባቻ ፀሐይ ለአሸበረቀ መልክህ እና ተክለ ቁመናው ለአማረ ቁመትህ ሰላምታ ይገባል፤ ንጉሥ ዳዊት ሆይ! ነብየ ልዑል ቅዱስ ዳዊት ሆይ! እንደአማረች በውኃ ዳር እንደአለች ዕንጨት ቅጥር ታላቅ በሆነ በተክልህ ቦታ ውስጥ (በገነት) በጸሎትህ ትከለኝ፡፡ |
| ፳፪. ሰላም ለፀአተ ነፍስከ ዘከመ ልማድ ወሥርዓት፤ ወለበድነ ሥጋከ ግኑዝ በልብሰ ርቱዕ መንግሥት፤ መኑ ሰብእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት፤ እስመ በእንተዝ ፍቁረ አምላክ ዳዊት፤ በሕገ መዋቲ ፍጡር ከደነከ መሬት፡፡ | 22. ለፀአተ ነፍስከ፡- በቀና የመንግሥት ልብስ ለተገነዘ የሥጋህ በድን እና እንደ ልማድና ሥርዓት ለነፍስህ መውጣት ሰላምታ ይገባል፤ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! ‹ሞትን የማያያት ሕያው ሆኖ የሚኖር ሰው ማነው!› |

፳፫. ሰላም ለመቃብሪከ ዘምዕዝት በአልው፣ ከመ ልማዳዊ ሕጎሙ ለቀደምት አበው፣ ዳዊት ጸሊ ቅድመ ገጸ አምላክ ሕያው፣ ከመ እድኃን እም እቅፍተ ፀር ዘእግሩ ከዋው፣ ወእመ ሥገርቱ ለብእሲ ጽልሕው፡፡

፳፬. ቃልየ አጽምዕ እግዚኦ ወለቡ ጽራኅየ፣ ወአጽምአኒ ቃለ ስዕለትየ፣ በእንተ ጸሎቱ ለዳዊት አርከ እግዚእየ፣ ወእገኒ ለከ በኵሉ ልብየ፣ እስመ አልቦ ኀጥእ ወጊጉይ ከማየ፡፡

፳፭. አዳም አበ ዓለም ወሄኖክ አበ ኖኅ፣ አብርሃም አበ ሙሴ ወዳዊት የዋህ፣ ወዘካርያስ ንጹሕ ተዘከሩኒ ለለጊዜሁ ቅድመ ገጸ ክርስቶስ መሲሕ፣ እስመ ሕይወት ትንባሌክሙ ለኀጥእ ርሱሕ፡፡

ኦ አምላከ ቅዱስ ዳዊት ዕቀበኒ ወአድኅነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርከ..... ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቡነ ዘበሰማያት…

✞ ✞ ✞

ስለዚህ ነገር የአምላክ ልጅ በሚች ፍጡር ሕግ መሬት ከደነህ እኮን!

23. ለመቃብሪከ፡- በቀደሙ አባቶች ሕግ ልማድ በሽቱ ለጣፈጠች መቃብርህ ሰላምታ ይገባል፣ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሆይ! እግሩ ቀልጣፋ ከሆነ ከጠላት እንቅፋት እድን ዘንድ ከሕያው አምላክ ፊት ለምንልኝ፣ ከሸንጋይ ሰው ወጥመድም አድነኝ፡፡

24. ቃልየ አጽምዕ እግዚኦ፡- አቤቱ ቃሌን ስማ፣ ጩኸቴንም አድምጥ፣ የአንደበቴንም ልመና አድምጠኝ፣ እንደ እኔ በደለኛና ኃጢአተኛ የለምና፡፡ ስለ ጌታየ ወዳጅ ስለ ቅዱስ ዳዊት ጸሎት በፍጹም ሀሳቤ እገዛለሁ፡

25. አዳም አበ ዓለም፡- ለጐስቋላ ኃጢአተኛ ልመናችሁ ሕይወት ነውና የዓለም አባት አዳም፣ የኖኅ አባት ሄኖክ፣ የሙሴ አባት አብርሃም፣ የዋህ ዳዊት እና ንጹሕ ዘካርያስ ኹላችሁ ከመሲሕ ክርስቶስ ፊት ኃጥእ ልጃችሁን እኔን በየጊዜው አስቡኝ፡፡

አቤቱ የቅዱስ ዳዊት አምላክ ሆይ! እኔን ባሪያህን..... ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ዘወትር በየጊዜውና በየሰዓቱ አድነኝ ጠብቀኝም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

አባታችን ሆይ…

✞ ✞ ✞